የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፩
አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፰ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 1
ADDIS ABABA 7th November 2013

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፺፰/፪ሺ፮ ዓ.ም.

የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.......ገፅ ፯ሺ፻፲፩

## CONTENTS

Regulation No. 298/2013

Public Service Employee's Transport Service Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation........ Page 7111

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፺፰/፪ሺ፮

## የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩)(ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፺፰/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ "የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች" ማለት በአዲስ አበባ የሚገኙ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችን እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሥሪያ ቤቶችን ሠራተኞች ያጠቃልላል፡፡

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 298/2013

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO ESTABLISH THE PUBLIC SERVICE EMPLOYEE'S TRANSPORT SERVICE ENTERPRISE

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 47(1)(a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Public Service Employee's Transport Service Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No. 298/2013".

2. **Definition**

In this Regulation "public service employees" include employees of federal government offices in Addis Ababa and the Addis Ababa City Administration offices.

ያንዱ ዋጋ
Unit price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazette P.O.box 80,001

፫. **መቋቋም**

፩/ የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

፬. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

የትራንስፖርት ሚኒስቴር የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

፭. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል፡፡

፮. **ዓ ላ ማ**

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ ለፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች በሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፤

፪/ ከፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች የሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ውጪ ለሌሎች ተገልጋዮች የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት፤

፫/ ከዓላማው ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሌሎች ሥራዎችን ማከናወን፡፡

፯. **ካፒታል**

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፩ ቢሊዮን (አንድ ቢሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፭ መቶ ሚሊዮን (አምስት መቶ ሚሊዮን ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

፰. **ኃላፊነት**

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፱. **ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ**

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

፲. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፰ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

3. **Establishment**

1/ The Public Service Employees Transport Service Enterprise (hereinafter the "Enterprise") is hereby established as a public enterprise.

2/ The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

4. **Supervising Authority**

The Ministry of Transport shall be the supervising authority of the Enterprise.

5. **Head Office**

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa.

6. **Objectives**

The objectives for which the Enterprise is established are:

1/ to provide transport service to public service employees during office opening and closing hours;

2/ to provide transport service to other users outside of office opening and closing hours;

3/ to engage in other activities related to its objectives.

7. **Capital**

The authorized capital of the Enterprise is Birr 1,000,000,000 (one billion Birr) of which Birr 500,000,000 (five hundred million Birr) is paid up in cash and in kind.

8. **Liability**

The Enterprise may not be held liable beyond its total assets.

9. **Duration**

The Enterprise is established for an indefinite duration.

10. **Effective Date**

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 7th day of November, 2013.

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት